የሰበር መ/ቁ. 23439

ቀን 28/9/98

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- የኮተቤ ብረታ ብረት መሣሪያዎች ፋብሪካ የአደራ ቦርዱ ነ/ፈጅ ቀረበ፣

መልስ ሰጭ፡- አቶ ስንታየሁ ዋለ ቀርቧል።

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው።

በመ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክሱ የቀረበው የደረጃ እና የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ በሚል ነው። አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው። አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል።

ችሎቱም በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሥራ ክርክሮች ምን አይነት ናቸው የሚለውን የሕግ ነጥብ መሠረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል።

ፌዴራል ጠቅላ... ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፈርማ
ቀን 12/10/98

ይህ ችሎት በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የውል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፤ አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ነው የሚባው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ቅጥም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤ በአንፃሩ አንድ የሥራ ክርክር የወል ሳይሆን የግል የሥራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሠራተኛ /ሠራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል።

መ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የደረጃ እና የደመወዝ ጭማሪ ይሰጠኝ በሚል ያቀረበው ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የሥራ ክርክር አይደለም። በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን አለው በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ው ሣ ኔ

- የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመ.ቁ.395/01/97 ነሐሴ 26 ቀን 1997 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 41769 ታህሣስ 27 ቀን 1998 ዓ/ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ይ

